# የፖሊስ ሪፖርት ፋይል ማድረግ በኮሮናቫይረስ ጊዜ

የሜትሮፖሊታን ፖሊስ ዲፓርትመንት (ኤም.ፒ.ዲ.) ተቋማት በዚህ ጊዜ ክፍት እንደሆኑ ይቆያሉ፣ ነገር ግን ሊመጣ ከሚችል ተጋላጭነትና የኮሮናቫይረስ (ኮቪድ-19) ስርጭት ለመከላከል፣ ኤም.ፒ.ዲ. ለማህበረሰባችን የምንሰጠው ከፍተኛ ጥራት ያለው አገልግሎት ሳይቋረጥ ተጋላጭነትን ለመገደብ የበኩሉ ያደርጋል።

ወንጀልን ሪፖርት ማድረግ ቢፈልጉ፣ በአካል ሪፖርት ማድረጉ ላያስፈልግዎ ይችላል ። የጥቃት-ያልሆኑ ወንጀሎች ወደ ኤም.ፒ.ዲ. ሰራተኞች በአካል ሳይመጡ ሪፖርት የሚያደርጉባቸው ሁለት መንገዶች አሉ፡

### የፖሊስ ሪፖርት በኦንላይን ፋይል ያድርጉ

**ኤም.ፒ.ዲ. አስቸኳይ-ላልሆኑ ክስተቶች ሪፖርት የሚደረግበት ከላይ ያለው QR ኮድ ስካን በማድረግ ወይም የሚከተለውን ድረገጽ በመጎብኘት https://mpdc.dc.gov/onlinepolicereport ማግኘት የሚቻል በኦንላይን ሪፖርት ማድረጊያ መሳሪያ አለው።**

### የፖሊስ ሪፖርት በቴሌፎን ፋይል ያድርጉ

በቴሌፎን ሪፖርቲንግ ዩኒት ሂደት የሚደረግባቸው የ 9-1-1 እና 3-1-1 የቴሌፎን ጥሪዎች ሰፍተዋል።

## የትኞቹን ክስተቶች ነው በኦንላይንና በቴሌፎን ሪፖርት ማድረግ የምችለው?

ወደ 3-1-1 ወይም 9-1-1 የሚደረጉ የቴሌፎን ጥሪዎች በቴሌፎን ሪፖርቲንግ ዩኒት (ቲ.አር.ዩ.) ሂደት ሊደረግባቸው ይችላል። ቲ.አር.ዩ. ከታች ላሉ ሁሉም ክስተቶች ሪፖርቶችን ይፈጥራል። እነዚህ ሪፖርቶች ልክ ሌሎች በአካል ሪፖርት የተደረጉ ክስተቶች እንደሚያገኙት መጠነ ሰፊ ክትትል ይደረግባቸዋል።

### ቴሌፎን ሪፖርቲንግ ዩኒት ብቻ

- የእንስሳት ንክሻዎች
- የክሬዲት ካርድ ማጭበርበር
- የሕዝብ/የግል ንብረት ማበላሸት
- ማጭበርበር
- ገጭቶ ማምለጥ (ሂት ኤንድ ራን)
- የማንነት ስርቆት
- የጉዳት (ኢንጁሪ) ሪፖርት
- በያይነቱ
- ከሱቅ መስረቅ
- የታመመ/የተጎዳ ሰው
- ቀላል ጥቃት
- የጠፉ መኪናዎች፣ ብስክሌቶች ወይም ታጎች (መለያዎች)
- ያለ መብት ንብረት መውሰድ
- የአካላዊ ጉዳት ማስፈራሪያዎች/ የቀላል ወንጀል (ሚስደሚነር) ማስፈራሪያዎች

### ቲ.አር.ዩ. ወይስ ኦንላይን

- በንብረት ላይ የሚደርስ ጉዳት
- የንብረት ውድመት
- የጠፉ ንብረት እና የጠፉ ታጎች (መለያዎች)
- ስርቆት 1 እና 2
- ከመኪና ውስጥ መስረቅ

### መቼ ነው 9-1-1 መደወል የሚኖርብኝ?

- ክስተቱ የጥቃት ወንጀል፣ በቤተሰብ-ውስጥ የሚደረግ ክስተት ወይም ጥፋት፣ መሳሪያ፣ ወይም ከባድ ቁስሎች ያለበት . . . ከሆነ
- ተጠርጣሪው ክስተቱ በተደረገበት ቦታ ወይም በአቅራቢያ ካለ . . .
- አስቸኳይ ነገር ሲያጋጥም፣ ወይም አስቸኳይ እርዳታ የሚፈልጉ ከሆነ . . .

**9-1-1 ይደውሉ ወዲያውኑ**

በመጀመሪያ ጥሪ ቃለ ምልልስ ሲደረግ በማንኛውም ሰአት የፖሊስ ምላሽ የሚያስፈልግባቸው ሁኔታዎች ካሉ በቴሌፎን-የሚያናግሮት ያለ ሰራተኛ ኦፊሰር ወደ ቦታው ይልካል።

**የከተማ አገልግሎቶችና መረጃን በቀን ለ24 ሰአታት ለማግኘት 3-1-1 ይደውሉ**